በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

*የ1996 በጀት ዓመት*

*የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት*

*አዲስ አበባ*
*ሐምሌ 1996*

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

## *የ1996 በጀት ዓመት*

## *የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት*

*አዲስ አበባ*
*ሐምሌ 1996*

## ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**


1. መግቢያ------------------------------------------------------- 1

2. የ1996 በጀት ዓመት ዕቅድ ይዘት ------------------------------------ 2

3. በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ ተግባራት -------------------------------- 3
   - 3.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ------------------- 3
   - 3.2 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስን በተመለከተ ----------------- 5
   - 3.3 የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት /DHS/ ፕሮጀክት ዝግጅት ---------------- 7
   - 3.4 Archive ማዘጋጀት ---------------------------------------------- 7
   - 3.5 የጽ/ቤቱን ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ዝግጅት ------------------------------- 8
   - 3.6 ጽ/ቤቱን በሰው ኃይልና በማቴሪያል ማደራጀት----------------------8
   - 3.7 ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎች ----------------------------------------10

4. የበጀት አጠቃቀም መግለጫ -------------------------------------------12

5. ያጋጠሙ ችግሮችና ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች ---------------------15

6. ማጠቃለያ-------------------------------------------------------18

እዝል 1፡- የቆጠራ ቦታ ካርታ የ1996 በጀት ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ

1. <u>መግቢያ</u>

ፈጣን ዕድገትና ልማትን በማስመዝገብ አገሪቱ ካለችበት ረሃብና ድህነት ለማላቀቅ እንዲቻል በተለያዩ ክፍለ ኢኮኖሚዎች ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘቡና ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተቀይሰው በተግባር በመተርጎም ላይ ናቸው። እነዚህን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ለመንደፍ የሚያስችሉና ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ዕቅዶችን ለመከታተልና ውጤታማነታቸውን ለመገምገም ወቅታዊ የሥነ-ሕዝብ መረጃዎች አስፈላጊ ናቸው።

የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ከላይ ለተጠቀሱትና ለሌሎች ተግባራት ጠቀሜታ ያላቸውን የሥነ-ሕዝብ መረጃዎች በቆጠራና በናሙና ጥናት የመሰብሰብ፣ የማጠናቀርና ለተጠቃሚዎች የማቅረብ ተግባርና ኃላፊነት የተጣለበት መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ጽ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ለሦስተኛ ጊዜ በ1999 ዓ.ም የሕዝብና ቤት ቆጠራን በማካሄድ ወቅታዊ የሆነ መረጃ ለማቅረብ፣ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓት በአገሪቱ ለመዘርጋት የሚያስችል መሠረታዊ ጥናቶችን ለማካሄድ ...ወዘተ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል።

በዚሁ መሠረት በ1996 በጀት ዓመት ሊሠሩ ከታቀዱት ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እና ሌሎች የጽ/ቤቱ ተጓዳኝ ሥራዎች መካከል በበጀት ዓመቱ የቆጠራ ቦታ ካርታ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፆችና መጠይቆች ዝግጅት ሲያካሂድ ቆይቷል። በተጨማሪም ጽ/ቤቱን በሰው ኃይልና በማቴሪያል የማደራጀት ሥራዎች ተሠርተዋል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች በዕቅዱ መሠረት በማከናወን የሚጠበቀውን ውጤት ማስገኘት እንዲቻል የማያቋርጥ ክትትልና ግምገማ የተደረገ ሲሆን በሥራ ሂደት ለተፈጠሩ ችግሮችም መፍትሔ ለመሻት ተገቢው ጥረት ተደርጓል።

በመሆኑም በ1996 በጀት ዓመት በጽ/ቤቱ የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ ይህ የግምገማ ሪፖርት ተዘጋጅቷል። ሪፖርቱ ስድስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነሱም መግቢያ፣ የ1996 በጀት ዓመት የጽ/ቤቱ ዕቅድ ይዘት፣ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ ሥራዎች፣ የበጀት አጠቃቀም፣ በሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች፣ ትኩረትና መመሪያ የሚያሻቸው ጉዳዮችን እና ማጠቃለያን አካቶ በያዘ መልኩ ተዘጋጅቷል።

## 3. በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ ተግባራት

### 3.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች

#### 3.1.1 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራን በተመለከተ

ከሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መካከል አንዱ እና ግዙፍ የሆነው የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ በ1995 በጀት ዓመት ከአንድ ሺህ በላይ የቆጠራ ካርታ ሠራተኞች ለሁለት ወራት ስልጠና በመስጠትና በ130 የቆጠራ ካርታ ቦታ ቡድኖች በማደራጀት በሁሉም ክልሎች የመስክ ሥራው ከተጀመረ በኋላ በበጀት እጥረት ምክንያት መቋረጡ የሚታወቅ ነው።

በ1996 በጀት ዓመት ከተፈቀደው የካፒታል በጀት ጋር በማጣጣም ሥራውን በአዲስ መልክ ለማስጀመር ሰፊ የሎጂስቲክስና የአስተዳደር ሥራዎች ተሠርተዋል። የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው ለአዲስ አበባ ቀረብ ባሉ የአገሪቱ ክልሎች ማለትም በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልሎች እንዲቀጥል ለማድረግ ቀደም ሲል ከሰለጠኑት ሠራተኞች መካከል የተወሰኑትን በመቅጠር በአዲስ መልክ የማሠማራት ሥራ ተሰርቷል። የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በ1995 በጀት ዓመት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ በአደራ መልክ የተረከባቸውን የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ የካምፕ ዕቃዎችና የመስክ ቁሳቁሶችን እንዲመልስ ለማድረግ ረጅም ጊዜ የፈጀ ክርክር አልፎም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጣልቃ እንዲገባበትና መመሪያ እንዲሰጥበት ከተደረገ በኋላ የመስክ እቃዎችን በመረከብ ቀጥሎም ለመስክ ሠራተኞች በማስረከብ ሥራው እንዲጀመር ተደርጓል። በዚሁ መሠረት:-

- የካርታው ሥራ እንደገና ከተጀመረበት ከነሐሴ 10/1995 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/1996 ዓ.ም ድረስ በ45 ቡድኖች 17,926 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ለማዘጋጀት ተችሏል። አፈፃፀሙ ከታቀደው 14,850 ( 45x30x11) የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ጋር ሲነፃፀር 20.7% ያህል ብልጫ ያለው ሥራ መሠራቱን ያመለክታል። ይህም ሊሆን የቻለው ለሠራተኞቹ ተገቢው ቁሳቁስ በወቅቱ እንዲቀርብ በመደረጉ፣ በመስክና በቢሮ ደረጃ ተገቢው ክትትል በመደረጉና ለተከሰቱ ችግሮችም ወቅታዊ ምላሽ በመስጠቱ ... ወዘተ ነው። ይሁን እንጂ በሀገሪቱ በጠቅላላው ይሠራል ተብሎ ከታቀደው 90,000 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች አንፃር ሲታይ የተከናወነው 19.9% ብቻ ነው፡፡ /ዝርዝሩ በዕዝል 1 ቀርቧል/።

- ለቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ የሚያስፈልጉ በርካታ የተለያዩ ቅፆች፣ ካርታዎችና የከተሞች ማስተር ፕላኖች፣ /ከተለያዩ መ/ቤቶች ዋናውን ቅጅ በአደራ መልክ በመረከብና በማሳተም/ በበቂ ቅጂ በማዘጋጀት እና አስፈላጊ የሆኑ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች በወቅቱ ተገዝተው ወደ መስክ እንዲሰራጩና በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።
- ምንም እንኳን እየተካሄደ ላለው የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ በቂ ባይሆንም ከUNFPA በዕርዳታ ተገዝተው የመጡ 24 ተሽከርካሪዎች ርክክብ ከተደረገ በኋላ አስፈላጊው የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተጠናቆላቸው ወደ መስክ እንዲሠማሩ ተደርጓል።
- የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው በዕቅዱና በተሰጠው መመሪያ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ መመሪያ ለመስጠት፣ የቴክኒክና አስተዳደራዊ ችግሮች ካሉ መፍትሔ ለመሻት እንዲቻል በየወሩ መጨረሻ የቆጠራ ካርታ አስተባባሪዎችን በመሰብሰብና ውይይት በማድረግ ተገቢውን መመሪያ በመስጠት እንደዚሁም በተለያዩ ጊዜያት የመስክ ጉብኝት በማድረግ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል። በተለያዩ ጊዜያት በዓመት ሁለት ጊዜ የማኔጅመንትና የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በአንድ ላይ በመቀናጀትና የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ እየተካሄደ ባለባቸው ቦታዎች በመሰማራት ባደረጉት የመስክ ጉብኝት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ መመሪያዎችን በመስጠት ተገቢው ክትትል ተደርጓል። ይህም አሠራር በበጀት ዓመቱ ለታቀዱት ሥራዎች በዕቅዳቸው መሠረት እንዲከናወኑ ለሚጠበቁ የቆጠራ ቦታ ካርታዎች በጥራት መሰራት የበኩሉን እገዛ አድርጓል።
- ከመስክ ተጠናቅቀው የሚመጡ የተለያዩ የቆጠራ ቦታ ካርታዎች፣ ለቤተሰብ ምዝገባና ለጂፒኤስ ኮኦርዲኔቶች ዝርዝር መረጃ ምዝገባ የሚሆን የዳታ ኢንትሪ ፕሮግራም ተዘጋጅቶ መረጃዎችን ኮድና ኤዲት በማድረግ ወደ ኮምፒውተር ማስገባትና ዲጂታይዝ የማድረጉ ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የ20 ወረዳዎች የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ዲጂታይዝ ተደርገው ዳታ ቤዝ ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የ100 ወረዳዎች የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽና የ12 ወረዳዎች የኮኦርዲቴቲንግ መመዝገቢያ ቅጽ ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ሥራ ተጠናቋል።
- የተጠናቀቁ የቆጠራ ቦታ ካርታዎችን እና ሌሎች ዶክመንቶችን በበቂ ኮፒ በማዘጋጀት ለዋናው ቆጠራ ለማስቀመጥ ታስቦ ከUNFPA በእርዳታ በተገኘ ገንዘብ ከውጭ ተገዝተው የመጡ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች አቅም አነስተኛ በመሆኑና በቦታ ጥበት ምክንያት በዕቅድ መሰረት መጠቀም አልተቻለም፡፡ ይሁንና ዶክመንቶቹ የተሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ የማደራጀቱ ሥራ ሲሠራ ቆይቷል። በዚሁ መሠረት ከተጠናቀቁት 109

ወረዳዎች መካከል የ102 ወረዳዎች የቆጠራ እና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎች ርክክብ ተፈፅሟል፡፡

### 3.1.2 የቆጠራ መጠይቆች ዝግጅትን በተመለከተ

የሦስተኛውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ መጠይቆች ለማዘጋጀት አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብና የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ካለፉት ቆጠራዎች የተሻለ ቴክኒካዊ ደረጃ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚረዱ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

ይኸውም ባለፉት ሁለት ቆጠራዎች ወቅት ሥራ ላይ የዋሉትን መጠይቆች ጠንካራና ደካማ ጎኖች ከቴክኒክ አኳያ በመገምገምና በቅርብ ጊዜ ቆጠራ ካካሔዱ ሌሎች አገሮች መጠይቆች፣ ተጠቃሚዎችን በማነጋገርና ከአለም አቀፍ ደረጃዎች /International standard/ ጋር በማገናዘብ የጥያቄዎችን አቀራረብና የመልስ አማራጮችን ለማሻሻል የሚረዱ ሪፖርቶች ተዘጋጅተዋል፡፡

በዚህም መሠረት የሕዝብ ብዛትና ባሕሪያትን፣ የቤቶች ሁኔታና የሰው ኃይልን፣ የልደትና፣ የሞትን፣ የፍልሰትና አሠፋፈርን እንዲሁም የትንበያ ስታቲስቲክስን በተመለከተ ሰፋ ያሉ ጥናቶችንና ግምገማዎችን በማካሄድ የሦስተኛውን ዙር ቆጠራ መጠይቆች ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡

## 3.2 የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስን በተመለከተ

እንደሚታወቀው የኮሚሽኑ ጽ/ቤት አንዱ ተግባር በሀገሪቱ ከሚዘረጋው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀርና በመተንተን በሀገር አቀፍና በክልል መስተዳድሮች እልፎም በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ለተለያዩ መረጃ ተጠቃሚዎች ዓመታዊ የልደት፣የሞት፣የጋብቻና ፍቺ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ማሰራጨት ነው፡፡ ለዚህም በቅድሚያ የምዝገባ ሥርዓቱ በሀገር አቀፍና በክልል መስተዳድሮች እንዲቋቋም ማድረግ ግድ ስለሆነ ጽ/ቤቱ የምዝገባ ሥርዓቱን ለማቋቋም የሚያስችሉ ቴክኒካዊ ጥናቶችን ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በጽ/ቤቱ ቀደም ሲል የተጀመሩ የጥናት ሥራዎችን ጥልቀት ባለው መልኩ በመመርመር የምዝገባ ሥርዓቱን ለማቋቋም የሚረዱ ቴክኒካዊ የአሠራር መመሪያ ረቂቆችን የማሻሻል

ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ እንደዚሁም በሀገሪቱ ስለወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ አሠራር በቂ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችል ጽሁፍ ለማዘጋጀት በተያዘው ፕሮግራም መሠረት አንድ መጽሄት ተዘጋጅቶ ለተለያዩ የፌዴራልና የክልል አካላት ተሠራጭቷል፡፡ ይኸውም በፌዴራል ደረጃ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በሥሩ ላሉ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ለፕሬስ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች፣ ለምርምር ተቋማት፣ እንዲሁም ለዘጠኙም የክልል መስተዳድሮችና ለአዲስ አበባና ድሬዳዋ መስተዳድር ጽ/ቤቶች፣ ለክልል ሥነ-ሕዝብ ጽ/ቤቶችና ለጤና ቢሮዎች ተሰራጭቷል፡፡

በሌላ በኩል የአማራና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በየክልላቸው የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ስርዓትን ለማቋቋም በሚያደርጉት ጥረት ጽ/ቤቱ አስፈላጊውን ቴክኒካዊ የምክር እገዛ አድርጓል። በተመሳሳይ ሁኔታ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲሰራበት የነበረውን የኩነቶች የምስክር ወረቀት የመስጠትን ልማዳዊ አሰራር ወደ አግባባዊ አሰራር ለማሻሻል በሚቻልበት መንገድ ላይ ጉዳዩ ከሚመለከተው የመስተዳድሩ የውልና የክብር መዝገብ አገልግሎት መ/ቤት ጋር በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም በመስተዳደሩ ሲሰበሰቡ የነበሩትና ወደ ኮምፒዩተር የገቡ የኩነቶች መረጃ መነሻ በማድረግ ከነሱ ሊወጣ የሚችል ስታትስቲካዊ መረጃ እንዳለ ለማወቅ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመጠቀም መረጃዎችን ለማጠናቀር ተሞክሯል። በዚሁ መሠረት ያለውን የመረጃ ችግር፣ ሊሆን ስለሚገባው አሠራርና የወደፊት አቅጣጫን ለመሻት እንዲረዳ በቀጣይነት በመረጃው ላይ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ነው።

በተጨማሪም ወሳኝ ኩነቶችን በተመለከተ በስድስት ርዕሶች ላይ ጥናታዊ ጽሑፎች በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅተዋል፡፡ ይኸውም፡-

ሀ/ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታትስቲክስ ሥርዓቶች ሕግን አስመልክቶ አንዳንድ ነጥቦች፣

ለ/ የወሳኝ ኩነቶች ስታትስቲክስ በዘመናዊው ዓለም የሚሰጡት ጥቅሞችና የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የወሳኝ ኩነቶች ስታቲስቲክስ ሥርዓትን በማቋቋም፣ በማደራጀትና በመምራት ረገድ ያለበት ኃላፊነትና ተግባር፣

ሐ/ የክብር መዝገብ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባና ስታቲስቲክስ ሥርዓቶችን አስመልክቶ አንዳንድ ነጥቦች፣

መ/ በኢትዮጵያ በሚቋቋመው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት የወሳኝ ኩነቶች

ስታቲስቲክስን እንዴት ማካተት ይቻላል ?

ሠ/ Project Proposal: Promotion, Awareness Creation and Capacity Building of CR and VS Systems.

ረ/ Variables and List of Tables for Vital Statistics.

በአገሪቱ ማዕከላዊ የወሣኝ ኩነቶች ምዝገባ ጽ/ቤት ለማቋቋም የወሣኝ ኩነቶች ምዝገባ ስርዓት ለማደራጀት በወጣው ረቂቅ አዋጅ ላይ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውይይት ተደርጎ ለዝርዝር እይታ ረቂቅ አዋጅ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መመራቱ ይታወሳል፡፡ ኮሚቴዎቹ ሙያውና ሥራው የሚመለከታቸው መ/ቤቶች በአዋጁ ላይ አስተያየት እንዲያቀርቡ በጠየቁት መሠረት ጽ/ቤቱ ሰፊና ጠለቅ ያሉ በጥናት ላይ የተመሠረቱ አስተያየቶችን በፅሑፍ አቅርቧል፡፡

## 3.3 የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት /DHS/ ፕሮጀክት ዶክመንት ማዘጋጀት

ለሁለተኛ ዙር በ1997 ሊካሄድ ለታሰበው የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት በተመለከተ ዝርዝር የሥራ ዕቅድና የበጀት ፍላጎት ያመላከተ የፕሮጀክት ዶክመንት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ ታቅዶ ነበር። ሆኖም የጥናቱን ወጪ በዋነኛነት የሚሸፍነው የዩናይትድ ስቴትስ የእርዳታ ሰጪ ድርጅት /USAID/ በመሆኑና ጥናቱንም በቴክኒክ በኩል የሚመራው አማካሪ ድርጅት በወቅቱ የኮንትራት ጊዜው በማለቁ ምክንያት በእርዳታ ሰጪ ድርጅቱ በኩል ሥራውን ማን እንደሚሰራው ገና ያልተወሰነ በመሆኑ የፕሮጀክት ዶክመንቱን ማዘጋጀት አልተቻለም። ይህንንም በመገንዘብ አማካሪ ድርጅቱ እስከሚታወቅ ድረስ በመጀመሪያው ዙር ጥናት በሥራ ላይ የዋሉትን መጠይቆችና መመሪያዎች እንደዚሁም የመስክ ሪፖርቶች በመፈተሽና በማጥናት የተወሰኑ ዝግጅቶችን ጽ/ቤቱ ሲያደርግ ቆይቷል።

## 3.4 Archive ማዘጋጀት

ቀደም ሲል የተካሄዱ የሁለት ቆጠራ ውጤቶችና የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት ውጤቶችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለመረጃ አያያዝና ለተጠቃሚዎች ምቹ የሆነ Archive ለማዘጋጀት የታቀደ ሲሆን ሥራው በአንድ ወቅት ተሰርቶ የሚያበቃ ስላልሆነ ቀደም ሲል ከተካሄዱት ቆጠራዎች ውስጥ የ1987 የቆጠራ መረጃ በዘመናዊ መልኩ ተዘጋጅቷል። ሌሎችም በቀጣይነት ለመስራት አንዳንድ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው።

## 3.5 የጽ/ቤቱ ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ዝግጅት

በአገሪቱ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በዕቅድ ላይ የተመሰረተ አመራር፣ ውጤታማ የዕቅድ አወጣጥና የአፈፃፀም መለኪያ ስልት ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ አማራጭ የሌለው መሆኑን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ መመሪያ ይገልጻል፡፡ በዚህ ረገድ የኮሚሽኑ ጽ/ቤት የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የሚያስችል ከ1997 እስከ 1999 የሚመራበትን ስትራቴጂካዊ ዕቅድ (SPM) በማዘጋጀት በሠራተኛው ከፀደቀ በኋላ ወደሚመለከተው የበላይ አካል ለመላክ ተዘጋጅቷል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ የጽ/ቤቱ ሠራተኞች ማበርከት የሚገባቸውን ውጤት በሚፈለገው መጠን፣ ጥራት፣ ጊዜና ወጪ በተሟላ ሁኔታ ማከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአፈፃፀም ሥርዓት /ውጤት ተኮር/ በመቅረጽ ሲሠራበት ቆይቷል።

## 3.6 ጽ/ቤቱን በሰው ኃይልና በማቴሪያል ማደራጀት

ሀ/ <u>የሰው ኃይል ቅጥርን በተመለከተ</u>

የሰው ኃይል አስተዳደርን በተመለከተ በጽ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ 104 ቋሚና 5 የኮንትራት ሠራተኞች በድምሩ 109 ሠራተኞች ነበሩ። በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ውስጥ 16 ቋሚና 364 የኮንትራት ሠራተኞች በድምሩ 380 ሠራተኞች ቅጥር የተፈጸመ ሲሆን 8 ቋሚና 20 የኮትንራት ሠራተኞች በድምሩ 28 ሠራተኞች በገዛ ፈቃዳቸው ተሰናብተዋል። በመሆኑም በኮሚሽኑ ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በአጠቃላይ 456 ሠራተኞች በሥራ ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ 112 ቋሚና 344 የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው። /ዝርዝሩ በሠንጠረዥ 1 ተመልክቷል/።

በአሁኑ ወቅት በጽ/ቤቱ ውስጥ ያለው የቋሚ ሠራተኛ ብዛት ቀደም ሲል ሲቋቋም ተፈቅዶለት ከነበረው 212 የሥራ መደቦች ጋር ሲነፃፀር 53% ብቻ መሟላቱን ያመለክታል። ይህ የሆነበት ምክንያት የሚፈለገው ባለሙያ በገበያ ላይ ያለመገኘት አንዱ ችግር ቢሆንም የጽ/ቤቱ ዋንኛውና ከፍተኛ ችግር የሆነው የቢሮ እጥረት በሠራተኛው ቅጥር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ ነው።

ሠንጠረዥ 1. የሰው ኃይል ስብጥር በቅጥር እና በሙያ ዓይነት

| የቅጥሩ ዓይነት | ፕሣ | | መፕ | | እስ | | ጽሂ | | አቶ | | ተጉ | | ድምር | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | |
| ቋሚ | 34 | 6 | 15 | - | 3 | 2 | 1 | 19 | 5 | - | 10 | 17 | 68 | 44 | 112 |
| ኮንትራት | 45 | - | 273 | 1 | - | - | 2 | 1 | 22 | - | - | - | 342 | 2 | 344 |
| ድምር | 79 | 6 | 288 | 1 | 3 | 2 | 3 | 20 | 27 | - | 10 | 17 | 410 | 46 | 456 |

ሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው የጽ/ቤቱ ቋሚ ሠራተኞችን አስመልክቶ ከሙያ አንፃር 40 ፕሮፌሽናሎች፣ 15 መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች፣ 57 የአስተዳደርና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ሲኖሩ የኮንትራት ሠራተኞችን በተመለከተ 45 ፕሮፌሽናሎች፣ 274 መለስተኛ ፕሮፌሽናሎች እና 25 የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ይገኛሉ። በተመሳሳይ መልኩ የሠራተኞች ስብጥር በፆታ ሲታይ ከቋሚ ሠራተኞች መካከል 68ቱ ወንዶች እና 44ቱ ሴቶች ሲሆኑ በኮንትራት ሠራተኞች በኩል ደግሞ 342ቱ ወንዶች እና 2ቱ ሴቶች ናቸው።

## ለ/ ሥልጠና

ጽ/ቤቱ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በአግባቡ በተግባር በመተርጎም የታሰበውን ውጤት ለማግኘት ይቻል ዘንድ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ያስፈልገዋል። ይህን ዓይነት የሰው ኃይል ለማፍራት ከሚቻልባቸው መንገዶች መካከል ሠራተኛውን በተለያዩ የትምህርት፣ የሥልጠና ፕሮግራሞችና አውደ ጥናቶች እንዲሳተፉ ማድረግ አንዱና ዋነኛው ነው። በዚህም መሠረት በበጀት ዓመቱ የጽ/ቤቱ ሠራተኞች በተለያዩ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞችና ልዩ ልዩ በአጫጭር የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችና አውደ ጥናቶች ላይ ተካፍለዋል፡፡ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፡-

- ስድስት የጽ/ቤቱ ሠራተኞችን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት በመከታተል ላይ ይገኛሉ። እንደዚሁም በውጭ ሀገር (በደቡብ አፍሪካ) ሁለት ባለሙያዎች በድህረ ምረቃ የትምህርት መስኮች በመሰልጠን ላይ ናቸው፡፡
- በተለያዩ ጊዜያት የሠራተኛውን አቅም ለማጎልበት በሚያግዙ ሥልጠናዎችና አውደ ጥናቶች ላይ 43 በጽ/ቤቱ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች እንደ የሙያ ቅርበታቸው እየተመዘነ እንዲካፈሉ ተደርጓል።

የሰው ኃይል ሰብጥር በቀጥር እና በሙያ ዓይነት

| ጠቅላላ ድምር | ድምር | | ጥቅ | | ለጉ | | ደረ | | ለበ | | መጥ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ |
| 112 | 44 | 68 | 17 | 10 | - | 5 | 19 | 1 | 2 | 3 | - | 15 | |
| 344 | 2 | 342 | - | - | - | 22 | 1 | 2 | - | - | 1 | 273 | |
| 456 | 46 | 410 | 17 | 10 | - | 27 | 20 | 3 | 2 | 3 | 1 | 288 | 6 |

... ላይ እንደሚያሳየው የጅቡቲ ቅርንጫፍ ሠራተኞችን አስመልክቶ ከሙያ አንፃር 46 ... ቶች፤ 15 መሐንዲሶች ፣ ቴክኒሻኖችና 57 የአስተዳደርና ልዩ ልዩ ሙያ ... ችን ያካተተ ሲሆን ... 224 ... 25 ... ሠራተኞች ... በተጨማሪም ... 68 ... 44 ... 342 ወንዶች እና 2 ሴቶች ናቸው።

...

... 342 ወንዶች እና 2 ሴቶች ናቸው።

- በሌላ በኩል በሁለተኛ ደረጃ ሙያና ቴክኒክ ት/ቤት የመጡ ሁለት የተማሪ ሰልጣኞች በጽ/ቤቱ በፋይናንስ ዋና ክፍል የሥራ ልምምድ ስልጠና ተከታትለዋል።

## ሐ/ ጽ/ቤቱን በቢሮና በማቴሪያል ማደራጀትን በተመለከተ

የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት በኪራይ እና የቀድሞ የኢትዮጵያ ችርቻሮ ንግድ ኮርፖሬሽን (ኢችንኮ)የነበረውን ቢሮ ከመንግሥት በመረከብ አነስተኛ ክፍሎች ባላቸው በእነዚህ ሁለት የተራራቁ ቢሮዎች ውስጥ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ ቢሮዎቹም ያረጁ በመሆናቸው ለዕድሳት ከፍተኛ ወጪ ከመጠየቃቸው በተጨማሪ ለማደስ የጠየቀው ጊዜም ቀላል አልነበረም፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ የተጠቀሱት ሁለት ቢሮዎች አሁን በሥራ ላይ ለሚገኙ ሠራተኞች እንኳ በቂ ክፍሎች የሌላቸው በመሆኑ ባሉት ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኞችን ቀጥሮ ማሠራት አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም በከፍተኛ ወጪ ተሠርተው ከመስክ ለሚመጡ የተለያዩ የቆጠራ ቦታ ካርታዎችና ቅጾች ማስቀመጫ መጋዘን ባለመኖሩ ዶክሜንቶቹን ሥርዓት ባለው መንገድ አደራጅቶ በማስቀመጥ ረገድ ከፍተኛ ችግር ተፈጥሮአል፡፡ ከዚህም በላይ በ1995 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ በሁሉም ክልሎች በ130 ቡድኖች ሲጀመር ለማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተሰራጭተው የነበሩትን የካምፕ ዕቃዎችና የመስክ መገልገያ ቁሳቁሶች ለመረከብ በቢሮ ዕጦት ምክንያት ከፍተኛ ችግር ገጥሞታል፡፡

## 3.7 ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎች

- በጽ/ቤቱ የ1995 የበጀት ዓመት የሥራ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣ ስለ 1996 ዓ.ም የሥራ ዕቅድና ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ጋር በተያያዘ የጽ/ቤቱ ሠራተኞችና ከፍተኛ የአመራር አባላት በቂ ውይይት እንዲያደርጉ የሚያስችል መድረክ በማመቻቸት የጋራ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተችሏል፡፡
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የሀገሪቱን የሶስት ዓመት የኢንቨስትመንት ፕሮግራም ለመቀየስ እንዲያስችለው የጽ/ቤቱ ከ1997 እስከ 1999 ዓ.ም ድረስ የሚያከናውነው የፕሮጀክት ሥራ እና የ1997 መነሻ ዕቅድ በተለይም ለሕዝብና ቤት ቆጠራ ፕሮጀክት የሚያስፈልገውን የካፒታል በጀት ፍላጎት እንዲያቀርብ በጠየቀው

መሠረት ተዘጋጅቶ ለሚኒስትር መ/ቤቱ ተልኳል፡፡

- የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ለኮሚሽኑ ጽ/ቤት እንደ የሥራ መደቡ ባህሪ ሊያገለግል የሚችል የደረጃ ዕድገት ማወዳደሪያ መመሪያ ጽ/ቤቱ እንዲያዘጋጅ በጠየቀው መሠረት የመመሪያው ረቂቅ ተዘጋጅቶ በጽ/ቤቱ የሥራ አመራር አባላትና ሠራተኞች ውይይት ተደርጎበት ለኮሚሽኑ ተልኮ ተግባራዊ እንዲሆን ከታመነበት በኋላ በጽ/ቤቱ ውስጥ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።
- ጽ/ቤቱ በአሁኑ ወቅት እያካሔደ ያለውንና በ1999 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ ለሚያካሂደው የ3ኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ግዙፍ ተግባር የሆነውን የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ እንቅስቃሴ በስፋት ለማስተዋወቅ የሚረዳና በየወቅቱ የሚታተም "ዜና ቆጠራ ካርታ" የዜና መጽሔት በማዘጋጀት የመጀመሪያውን ዕትም አሰራጭቷል፡፡
- የጽ/ቤቱን አመሠራረት፣ የተቋቋመባቸውን ሁለት ዓቢይ ዓላማዎችና የ3ኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የቅድሚያ ተግባር የሆነውን የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን በማስተዋወቅ ተከታታይነት ያለው ሥራ ተሠርቷል፡፡ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ብሮሸር ተዘጋጅቶ ተሰራጭቷል፡፡
- በማስታወቂያ ሚኒስቴር አስተባባሪነት በሃገሪቱ ያለውን የሕዝብ ግንኙነትን አሠራር በተጠናከረ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልክ እንደገና ለማደራጀት በተዋቀረው የረቂቅ ደንብ ዝግጅት ውስጥ ጽ/ቤቱ በንቃት በመሳተፍ ላይ ይገኛል፡፡
- ለ32 ተሽከርካሪዎችና ለ375 የመስክ ሠራተኞች፣ (ሾፌሮች፣ ተቆጣጣሪዎች እና የአመራር አባላት) የኢንሹራንስ ዋስትና በተገባላቸው መሠረት አደጋ ለደረሰባቸው ተሽከርካሪዎች ለመድን በወቅቱ ሪፖርት ቀርቦ ተገቢውን ጥገና እንዲያገኙ ተደርጓል። አደጋ የደረሰባቸው ሁለት የመስክ ሠራተኞች የሕክምና ወጪ በመድን እንዲሸፈን ተደርጓል።
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ፣ የተሽከርካሪዎች አጠቃቀምና የተዛማጅ መዝገብ አያያዝ ኦዲት ሥራን አስመልክቶ የ1996 በጀት ዓመት የ9 ወራት የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃቀም ንጽጽር...ወዘተ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ እንደዚሁም ካለፈው በጀት ዓመት የዞሩ ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የቀረቡ ሂሳቦች ላይ የቅድመ ምርመራ በማካሄድ እንዲወራረዱ የተደረገ ሲሆን የጽ/ቤቱ የገቢና ወጪ ሂሳብ እንቅስቃሴ በየወሩ የመመርመርና ማስረጃዎቹን የማስታረቅ ሥራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡
- የጽ/ቤቱ የተለያዩ የሥራ እንቅስቃሴዎች ባለው ደንብና መመሪያ መሠረት

እንዲከናወኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሲደረግ የቆየ ሲሆን በተለይም ለቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ የሚደረጉ ወጪዎች በተያዘላቸው ፕሮግራሞች ወጪ የማድረግ እንደዚሁም ሒሣቦቹን በወቅቱና በአግባቡ በውስጥ ኦዲት የማስመርመርና የማወራረድ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

- የአፍሪካ አካባቢያዊ ሁኔታ /Environmental Situation/ ያለበትን ደረጃ በመረዳት ዘላቂነት ያለው ልማትና ዕድገት ለማምጣት እየተደረገ ባለው ጥረትና በአካባቢ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ኡጋንዳ ካምፓላ ላይ በተደረገው ዘጠነኛው ስብሰባ የሚኒስትሮች ስብሰባ በአፍሪካ ደረጃ አንድ አህጉራዊ የአካባቢ መረጃ መረብ /Africa Environental Information New work/ እንዲቋቋም መወሰኑ ይታወቃል። በዚህ ውሳኔ መሠረት ከአፍሪካ ኢትዮጵያን ጨምሮ 13 ሀገራት ለሙከራ የተመረጡ ሲሆን በአገሪቱ ደረጃ ኃላፊነት ከተሰጠው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አስተባባሪነት ሥራውን ለመሥራት በተቋቋመው አገር አቀፍ የቴክኒክ ኮሚቴ ውስጥ ጽ/ቤቱ የነቃ ተሳትፎ ሲያደርግ ቆይቷል።
- የጽ/ቤቱ ሙያዊ ድጋፍና በተለይም ሕዝብንና ቤትን የተመለከቱ መረጃዎችን በመፈለግ ከዩኒቨርስቲዎች፣ከኮሌጆችና ከልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚመጡ መረጃ ፈላጊዎችን በአግባቡ በማስተናገድ የሚፈለጉትን መረጃና ሙያዊ እገዛ በወቅቱ እንዲያገኙ ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ ካለበት ከፍተኛ የቢሮ ጥበት የተነሳ በብዙ ምርምርና ጥናት የተዘጋጁ ጠቃሚ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ መረጃዎችን በተሟላና በተደራጀ የቤተመፃሕፍት አገልግሎት ደንበኞችን ማስተናገድ አልተቻለም፡፡

## 4. የበጀት አጠቃቀም መግለጫ

በ1996 በጀት ዓመት ጽ/ቤቱ ለማከናወን ላቀዳቸው ሥራዎች ማስፈፀሚያ በመደበኛ በጀት ብር 3,035,300 /ሦስት ሚሊዮን ሰላሳ አምስት ሺ ሦስት መቶ ብር/ እና የካፒታል በጀት ብር 10,000,000 /አሥር ሚሊዮን ብር/ በድምሩ ብር 13,035,300 /አሥራ ሦስት ሚሊዮን ሰላሳ አምስት ሺ ሦስት መቶ ብር/ ተመድቦለት ሥራውን ሲያከናውን ቆይቷል። በዚሁ መሠረት የዚሁ የበጀት አጠቃቀም እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 4.2. የካፒታል በጀት አጠቃቀም

ከላይ እንደተጠቀሰው ለዓመቱ ለፕሮጀክቱ ሥራ ማለትም ለቆጠራ ካርታ ሥራና ለሌሎችም ተጓዳኝ ሥራዎች ማስፈጸሚያ ከተፈቀደው ካፒታል በጀት ብር 10,000,000 /አሥር ሚሊዮን / ውስጥ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቶ የተለቀቀው ብር 8,130,540 /ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰላሳ ሺ አምስት መቶ አርባ ብር/ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ ብር 7,050,280 /ሰባት ሚሊዮን ሃምሳ ሺ ሁለት መቶ ሰማንያ ብር/ ወጪ ተደርጓል። ከዚሁ ውስጥ ከፍተኛውን ወጪ የያዙት ለኮንትራት ሠራተኞች ለውሎ አበል ብር 3,405,028 /ሦስት ሚሊዮን አራት መቶ አምስት ሺ ሃያ ስምንት ብር/ እና ለደመወዝ የተከፈለው ብር 1,620,623 /አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሺ ስድስት መቶ ሃያ ሦስት ብር/ ወጪዎች ናቸው። የበጀት አፈፃፀሙን በተመለከተም በሥራ ላይ የዋለው መጠን ለዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 70.5% ወጪ የተደረገ መሆኑን የሚያሣይ ሲሆን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቶ ከተለቀቀው ጋር ሲነፃፀር ደግሞ 86.7% ወጪ መሆኑን ያሳያል።

ለካፒታል በጀት አፈፃፀም ዝቅተኛ መሆን ዋና ዋና ምክንያቶች፦

- የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው በተለያዩ ምክንያቶች ከታቀደለት ጊዜ ከአንድ ወር በላይ ዘግይቶ በመጀመሩ፣
- የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው ለመሥራት 50 ቡድኖችን እንደሚዋቀሩ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በተሽከርካሪ እጥረት ምክንያት 45 ቡድኖች ብቻ በመዋቀሩ እና ለነዚሁ ቡድኖች ለሥራ ማስኬጃ የተያዙት ማለትም ለደመወዝ፣ ለውሎ አበል፣ ለነዳጅና ለተለያዩ ወጪዎች ተይዞ የነበረው በጀት ሥራ ላይ ባለመዋሉ፣
- ከUNFPA በዕርዳታ የተገኙና የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች በሙሉ አዲስ በመሆናቸው የነዳጅ ፍጆታቸውና የጥገና ዕድሳት ወጪያቸው ከተገመተው በታች ሆኖ መገኘት ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ለጽ/ቤቱ ለበጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈፀሚያ ከተመደበው ከብር 13,035,300 ጋር ሲነፃፀር 88.9 ከመቶ እንደተከናወነ ለመገንዘብ ይቻላል። ይህም ከላይ የተገለጹት ሁኔታዎች /የመኪና እጥረት፣ የሠራተኛ ቢሮ ያለመሟቸቸትና ቅጥር ያለመፈፀም/ ቢሟሉ ኖር ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ማዋል ይቻል እንደነበር ያመለክታል።

## 5. ያጋጠሙ ችግሮችና ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች

### 5.1 ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

- የ1996 በጀት ከተፈቀደ በኋላ ተቋርጦ የነበረውን የቆጠራ ካርታ ሥራ በሐምሌ ወር 1995 ሁለተኛ ሳምንት መጀመሪያ ለማስጀመር ታቅዶ ነበር። ነገር ግን የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በአደራ የተረከበውን የመስክ መገልገያና የካምፕ ቁሳቁሶች ጽ/ቤቱ መልሶ ለመረከብ ያደረገው ጥረት ረጅም ጊዜ የወሰደ በመሆኑ ወደ አንድ ወር የሚጠጋ የሥራ ጊዜ ባክኗል። በመጨረሻም ለበላይ አካል ሪፖርት በመደረጉ መመሪያ ተሰጥቶበት ችግሩ መፍትሔ ሊያገኝ ችሏል።
- ጽ/ቤቱ ሥራውን እያከናወነ ያለው በቂ ክፍሎች በሌላቸው ሁለት አነስተኛ እና በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ ቢሮዎች ውስጥ በመሆኑ በሥራው ፍጥነትና ቁጥጥር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሣድሯል። እንዲሁም ከመስክ ተጠናቅቀው የሚመጡ የተለያዩ ካርታዎችና ዶክመንቶች ማስቀመጥ አልተቻለም፡፡ ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች የሚመጡ በርካታ የካምፕና የመስክ መገልገያ ቁሳቁሶችን ተቀብሎ ለማስቀመጥ ከፍተኛ ችግር ፈጥሮ ነበር፡፡ ሆኖም ለመጋዘን የሚሆን ቆርቆሮ በቆርቆሮ በመስራት ለጊዜውም ቢሆን ችግሩን ለመቅረፍ ተሞክሯል።
- በአንዳንድ አካባቢዎች በቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራው ላይ በድንበር ጭቅጭቅ ምክንያት የሥራ ቀናት እየባከኑ በመሆናቸው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የወረዳና የቀበሌ መስተዳድር አካላትና ከሕብረተሰቡ ጋር ግንኙነት በመፍጠር መፍትሔ ለማግኘት ጥረት የተደረገ ቢሆንም በተወሰኑ አካባቢዎችና ወረዳዎች ከአቅም በላይ እየሆነ ጉዳዩ እልባት እስከሚያገኝ ሥራው እየተቋረጠ ከብዙ ጥረት በኋላ እንዲቀጥል ይደረጋል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ እንዳይደጋገምና የሥራ ቀናት እንዳይባክኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ሲደረግ ቆይቷል፡፡
- ለቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ እስከ መጨረሻ ድረስ ያገለግላሉ ተብለው የተገዙ የሸራ አልጋዎች ባልተጠበቀ ሁኔታ ተበላሽተው /ተበላስተው/ የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠት አልቻሉም። ለጊዜያዊ መፍትሔ ይሆን ዘንድ ቡድኖቹ በየአካባቢያቸው አስጠግነው እንዲጠቀሙ የተደረገ ቢሆንም ከየቦታው የሚቀርቡ የጥገና ወጪዎች የተለያዩ በመሆናቸው ሂሣብ በማወራረድ ረገድ ችግር ከመፍጠሩም በላይ ለዘለቄታው

አንድ ወጥ በሆነ መንገድ በጥራት ተጠግነው ሥራ ላይ እንዲውሉ 400 አልጋዎች ለቃሊቲ ብረታ ብረት ፋብሪካ ለጥገና ተሰጥተው ከነዚህ መካከል 50ዎቹ ተጠግነው ገቢ ሆነዋል።

## 5.2 ትኩረትና መመሪያ የሚያሻቸው ጉዳዮች

- የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 180/91 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 7 ላይ " የቆጠራ ካርታ ሥራ ወይም ቆጠራ ለማካሄድ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ሠራተኞች፣ ንብረትና አገልግሎት የመጠቀም..." የሚል በግልፅ የተቀመጠ ይገኝበታል፡፡ ይህንኑ መሠረት ከማድረግ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤትን ጨምሮ ለስምንት የተለያዩ መ/ቤቶች የመኪና የትብብር ደብዳቤ ቢፃፍም አዎንታዊ ምላሽ አልተገኘም፡፡

  ይህም ሆኖ ጽ/ቤቱ የቆጠራ ካርታ ሥራው እስከአሁን ከውጭ በዕርዳታ ባገኛቸው 24 የመስክ ተሽከርካሪዎች በመጠቀም እየሰራ ይገኛል፡፡ ሆኖም እነዚህ ተሽከርካሪዎች ለ45 ቡድኖች በቂ አይደሉም፡፡ በመሆኑም በሁለት ወረዳዎች ለተሠማሩ ለሁለት ቡድኖች አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ተመድቦ ሥራው በመካሄድ ላይ ስለሚገኝ አንድ ቡድን በመኪና ተጠቅሞ የሚሠራው በጣም አነስተኛ ለሆኑ ቀናት ብቻ ነው። እያንዳንዱ ቡድን መኪና ቢመደብለት ኖሮ አሁን ከሚሠራው ሥራ የበለጠ መሥራት ይችል እንደነበር ለመገመት አያዳግትም ። ከሌላም አንጻር የመኪና እጥረት ባይኖር ኖሮ ለዓመቱ የተፈቀደው በጀት ቢያንስ 50 ቡድኖችን ሊያሠራ ይችል ነበር። ስለሆነም የጉዳዩን አሳሳቢነት የሚመለከተው አካል ተረድቶት ተጨማሪ ሽከርካሪዎች የሚገኙበት ሁኔታ ቢመቻች።

- የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ራሱን ችሎ እንዲቋቋም ሲደረግ ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን መ/ቤት ከወጡት የሥራ ዘርፎች ጋር የተያያዙ የግል መገልገያ ንብረቶች (ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ የግል ኮምፒዩተር...ወዘተ) በስተቀር ሕጋዊ የሆነ የንብረት ክፍፍል አልተደረገም።

  ህዳር 14/96 በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በጠራው የጋራ ስብሰባ ላይ (የኮሚሽኑ ጽ/ቤቱ፣ የማ.ስ.ባ እና የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት በተገኙበት) የኮሚሽኑ ጽ/ቤት ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ጋር

ችግሩን አስመልክቶ ውይይትና የመፍትሔ ሃሳብ እንዲያቀርቡ በተወሰነው መሠረት ጽ/ቤቱ የተለያዩ ጥረቶች ቢያደርግም በወቅቱ መፍትሔ አልተገኘም፡፡ ይህም በወቅቱ በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንዲያውቀው ተደርጓል፡፡ ስለሆነም የንብረት ክፍፍሉ ተግባራዊ እንዲሆን አሁንም ትኩረት እንዲሰጠው እንጠይቃለን፡፡

- ጽ/ቤቱ ከፍተኛ የቢሮ ጥበት ስላለበት በሥራው ላይ እንቅፋት እየፈጠረበት ይገኛል፡፡ በተለይም በከፍተኛ ወጪ እየተሠሩ ያሉትን ካርታዎችና ዶክመንቶችን ሥርዓት ባለው መንገድ አደራጅቶ ለማስቀመጥ ካለመቻሉም በላይ በየጊዜው ተሰርተው የሚመጡትን ለማስቀመጥ ችግሩ የበለጠ እየከፋ ይገኛል፡፡ በዚሁ የቢሮ ጥበት ምክንያት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት እና የሥነምግባር መኮንን ሊኖረን አልተቻለም፡፡ የዕቃ ማከማቻ ባለመኖሩና ቢሮዎች የዕቃ ማከማቻ በመሆናቸው ሠራተኛው ሥራውን በአግባቡ ለማከናወን አልቻለም፡፡ ስለሆነም የሚመለከተው አካል አፋጣኝ መፍትሔ ሊፈልግለት ይገባል፡፡
- በ1999 በጀት ዓመት ለሦስተኛ ጊዜ የሚካሄደውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ ከግብ ለማድረስ ከቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለው የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ ሲሆን በመላ ሀገሪቱ 90,000 የሚሆኑ የቆጠራ ቦታ ካርታዎች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ በወቅቱ ተጠናቆ ለዋናው ቆጠራ ዝግጁ እንዲሆን በጽ/ቤቱ ዕቅድ መሰረት ከ1997 በጀት ዓመት ጀምሮ ቢያንስ 100 ቡድኖች ያካተተ የሰው ኃይል መስክ ለማሰማራት አስፈላጊውን ሎጅስቲክስና ትራንስፖርት ማሟላት ግዴታ ይሆናል፡፡ ሆኖም ለ1997 በጀት ዓመት ከተጠየቀው በጀት ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘውና በአሁኑ ወቅት በጽ/ቤቱ ሥራ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ እያደረሰ ያለው የተሽከርካሪ በጀት አልተፈቀደም። በመሆኑም ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደውን በጀት በአግባቡ በመጠቀም ሥራውን በሚፈለገው ሁኔታ ለማስኬድ አይቻልም። በተጨማሪም የቆጠራ ካርታ ሥራው መጠናቀቅ ከሚገባው ጊዜ በላይ እንዲጓተት ያደርጋል። እንደዚሁም በቀሩት ዓመታት የበጀት ፍላጎትን ከማናሩም በላይ የመስክ ሠራተኞች ስምሪት፣ የሥራ ጥረት ክትትልና ቁጥጥርን አስቸጋሪ ያደርገዋል። ስለሆነም ከላይ እንደተገለፀው በጀቱ የተዘጋጀው የሥራው ስፋትና የሚሰማራው ግዙፍ የሰው ኃይል ከግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን ይህንኑ የተሽከርካሪ ጉዳይ በሚመለከተው አካል ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጠው በአጽንኦት እንጠይቃለን።

## 6. ማጠቃለያ፦

የኮሚሽኑ ጽ/ቤት በበጀት ዓመቱ ለመሥራት ካቀዳቸው እና ከአከናወናቸው ሥራዎች መካከል የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ፣ ጽ/ቤቱን በሰው ኃይልና በማቴሪያል ማደራጀት፣ የጽ/ቤቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት...ወዘተ ይገኙበታል።

በዕቅዱም መሠረት በተደረገው ከፍተኛ ጥረት ለአጭር ጊዜ ተቋርጦ የነበረው የቆጠራ ቦታ ካርታ ሥራ እንደገና ተጀምሮ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትም በመረሀ-ግብሩ መሰረት ተከናውነዋል። ሠራተኞችን በተለያዩ ስልጠናዎችና አውደ ጥናቶች ላይ በማሳተፍ ብቃታቸው እንዲጎለብት ተደርጓል።

በሥራው ሂደት በአንዳንድ ቦታዎች የተከሰቱ የድንበር ጭቅጭቆች፣ የሰው ኃይልና የተሽከርካሪ እጥረት፣ የቢሮ ጥበት፣...ወዘተ ችግሮችን በመቋቋምና ጊዜያዊ መፍትሔ በመሻት ጽ/ቤቱ አቅሙ በፈቀደለት መጠን በመንቀሳቀስ ሥራዎቹን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን ይኸው ጥረት በ1997 በጀት ዓመት በይበልጥ በማጎልበት የሚቀጥል ይሆናል።

# የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የ1996
# የበጀት ዓመት የቆጠራ ቦታ ካርታ የሥራ እንቅስቃሴ

አዝል 1፦

| ክልል | የዞን ብዛት | የተጠናቀቁ ዞኖች | | የወረዳ ብዛት | የተጠናቀቁ ወረዳዎች | | የከተማ ብዛት | የተጠናቀቁ ከተሞች | | ጠቅላላ** የተጠናቀቁ የቆጠራ ቦታዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | በመቶኛ | | ብዛት | በመቶኛ | | ብዛት | በመቶኛ | |
| አፋር | 5 | - | - | 29 | - | - | 43 | - | - | - |
| አማራ | 11 | 1 | 9.0 | 106 | 19 | 17.9 | 209 | 35 | 16.7 | 2181 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 3 | - | - | 20 | - | - | 20 | - | - | - |
| ጋምቤላ | 2 | - | - | 9 | - | - | 9 | - | - | - |
| ሐረር | - | - | - | 1 | - | - | 1 | - | - | - |
| ኦሮሚያ | 15 | 5 | 33.3 | 193 | 62 | 32.1 | 377 | 130 | 34.4 | 9196 |
| ሶማሊያ | 9 | - | - | 51 | - | - | 81 | - | - | - |
| ደቡብ ብ/ብ/ሕ | 13 | 4 | 30.8 | 104* | 30 | 28.8 | 152 | 49 | 32.2 | 6549 |
| ትግራይ | 5 | - | - | 34 | - | - | 76 | - | - | - |
| አዲስ አበባ | - | - | - | - | - | - | 1 | - | - | - |
| ድሬዳዋ | - | - | - | 1 | - | - | 1 | - | - | - |
| ድ ም ር | 63 | 10 | 15.9 | 548 | 111 | 20.3 | 970 | 214 | 22.1 | 17,926 |

ማሳሰቢያ፦

* ልዩ ወረዳዎችን ይጨምራል

** መረጃው የሚመለከተው እስከ ሰኔ 30/1996 ድረስ ያለውን ነው።